የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No. 26
ADDIS ABABA, 7th July, 2023

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፭/፪ሺ፲፭

በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በግራንድ ዱች ኦፍ ሉግዘምበርግ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ....................ገጽ ፲፬ሺ፯፻፷፯

## Content

Proclamation No. 1295/2023

Convention between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and The Grand Duchy of Luxembourg for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation..................................... .Page 14767

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፭/፪ሺ፲፭

**በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በግራንድ ዱች ኦፍ ሉግዘምበርግ መንግሥት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በግራንድ ዱች ኦፍ ሉግዘምበርግ መንግሥት መካከል በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችል ስምምነት ሰኔ ፳፪ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም በሉግዘምበርግ የተፈረመ በመሆኑ፤

### PROCLAMATION NO. 1295/2023

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE CONVENTION BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GRAND DUCHY OF LUXEMBOURG FOR THE AVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION AND THE PREVANTION OF FISCAL EVASION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME**

**WHEREAS,** a convention for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income was signed between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Grand Duchy of Luxembourg on the 29th of June, 2021 in Luxembourg;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ይህን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፪ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአካሄደው ፳፫ኛ መደበኛ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ “በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በግራንድ ዱች ኦፍ ሉግዘምበርግ መንግሥታት መካከል የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፭/፪ሺ፲፭” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በግራንድ ዱች ኦፍ ሉግዘምበርግ መንግሥት መካከል ሰኔ ፳፪ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም በሉግዘምበርግ የተፈረመው በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችለው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 23rd ordinary session held on 30th Day of May, 2023;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the “Convention between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Grand Duchy of Luxembourg for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation No 1295/2023”.

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Convention between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Grand Duchy of Luxembourg for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with respect to Taxes on Income signed on the 29th of June, 2021 in Luxembourg is hereby ratified.

፫. <u>**የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን**</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር አግባብ ከአላቸው አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to implement the Convention in cooperation with the concerned government organs.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, On this 7th Day of July, 2023.**

**SAHLE-WORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**